


# ሚዛኗ የት አለች?

ሥርጉተ ሥላሴ

ለዓላማዋ አደራ፣ እድፍ ታጠራለች
ዕብለትን ሰንጋ፣ ለሀቅ ተሰውታለች
ሰንደቅን አድምቃ፣ ትውፊት ታፈልቃለች
ትናንት እና ዛሬ እሷ ትቀልጣለች።

**ሚዛኗ  የት አለች?**

ዓይናማ በመሆን፣ ፈር ቀዳጅ ሆናለች
መሆንን በመቻል፣ በተግበር ከብራለች
ዕናትን አቅልማ፣ ትግስት አጥብታለች
ከብርቱካን ጋራ ይኸው ተጋብታለች።

**ሚዛኗ የት አለች?**

ቃሏን በመጠበቅ፣ ቋሳን ፈትሻለች
እንክርዳድ ከስንዴ አንተርትራዋለች
ፋሽስተን አጋልጣ፣ ቀያፋን ልጋለች
ሰንሰለት ላይ ሆና ብርሀን ልካለች።

**ሚዛኗ የት አለች?**

አንድነት ፀንሳ አብሮነት ወልዳለች
ቀድማ በመገኘት ደወል ደውላለች
እራሷን ሰጥታ ጧፉን ለኩሳለች
ብርቱካን ፍሬዋን ይሄው አፍርታለች።

**ሚዛኗ የት አለች?**

የተበተነውን ልቦና ገርታለች
ትግሉነን በመኳል፣ መቀነት ታጥቃለች
ለኢትዮጵያዊነት ኪዳኑ፣ ድርሳኑ፣ ቀለበት ሆናለች
ብርቱካን እመቤት ለኛ ትሆናለች።

…2

**ሚዛኗ የት አለች?**

ክህሎትን በዕድምታ ትመግበናለች
በህሊና መንፈስ ታታግለናለች
ተስፋነን አብቅላ በአንድነት መርታለች
ፍቅርን ሸማ ሠርታ በምዕላት ድራለች

**ሚዛኗ የት አለች?**

ጨረሯ ዓለም ሆኖ ጢፉን ለኩሳለች
ለሙያዋ ፍቅር ልዩ ዓምድ ሆናለች
ከዳኛዋ ዘንዳ ከሷ ትገኛለች
ከብርቱካን ጋራ አብራ ተፈጥራለች።

**ሚዛኗ የት አለች?**

የእማን ጡት ፅንሷ አድርጋለች
ከብርቱካን ጋራ ዕውነት ገብራለች
ለሀገሯ ትንሳኤ ትንገበገባለች
በፈርኦን እግረ ብረት ትርገበገባለች።

**ሚዛኗ የት አለች?**

ሀቅን ትፈትላለች
ሞትን ሳትፈራ ቅደመኝ ብላለች
የወሰነችውን፣ የቆረጠችውን ትቆረጥማለች
ዕጣችን - ክፍላችን ንባችን ሆናለች።

**ሚዛኗ የት አለች?**

የግንባር ሥጋዋ እሷ ትሆናለች
ከጣይቱ ዘንዳ መክሊትን ወርሳለች
ፀጋችን በመሆን ቁርጡን ነገራናለች
የሲና ወርቅ ሆና ሁሌ ታበራለች።

**ሚዛኗ የት አለች?**

የቀዘቀዘውን እሷ ታደምቃለች
ምርኩዛችን ሁና ትደግፈናለች
ትውልዱን በተግባር ታደራጀዋለች
ብርቴ እሷ ለኛ ሆናለች።

በዓይነ ህሊና ትመጣብናለች
በመንፈስ ሰንሰለት ትናኘናለች
በአንድነት ድልድይ መንገዱን መርታለች።

የአንሰት አብነት ሀውልትም ሆናለች
ሥረ ጉባኤአችን፣ ቅኔአችን ቃናችን ...
ዳኛችን ሆናለች!

*ሥጦታ፣ ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአድነት ሊቀመንበር*
*ታህሣሥ 29 ቀን 2001 ዓ.ም, ሂርሽን ሆቴል*